# ሆሊውድ በገሃድ

በሳሙኤል ኀበደ




2




በyouthfocus የቴሌግራም ቻናል አየተዘጋጀች የምትቀርብ ሁለተኛ መጽሄታችን በሆኪውድ ዙሪያ የምትዳስስ ናት መልካም ንባብ።

ሳሙኤል ክበደ

# ሆሊውድ በገሃድ

የሆሊውድ ከተማ አመሰራረት ወደ 19ኛው ክፍለ ዘመን ይወስደናል የተመሰረተው እ.ኤ.አ በ1853 ወደ ሎስአንጀለስ ካሊፎርኒያ መኖሪያቸውን በቀየሩ ቤተሰቦች ነው። ቦታው የሚታወቀውም በሰብል ምርቱ ነበር። በ20ኛው ክፍለ ዘመን መግቢያ ላይ የነበረው የህዝብ ቁጥር 500 ሲሆን፤ አንድ ፖስታ ቤት አንድ ሆቴል እና ሁለት የገበያ ስፍራዎች ነበሩት። እ.ኤ.አ በ1900 አካባቢ የፊልም ባለሙያዎች በቶማስ ኤዲሰን ተንቀሳቃሽ ምስል የአእምሮ ንብረት ጥበቃ ተቋም አማካኝነት ከሚጣልባቸው ጠንካራ ህግ ለመሸሽ ወደዚህ ስፍራ መጉረፍ ጀመሩ። የመጀመሪያውን ተንቀሳቃሽ ምስል በዚያን ጊዜ የሰራው ቶማስ ኤድሰን ስለ ነበር የእሱን ስራ እንዳይሰርቁት በጣም ከባድ ህግ ያወጣባቸው ነበር።

የእርሱን ቁጥጥር ለመሸሽ ሲሉ እንደገናም ደግሞ በሆሊውድ አካባቢ በነበረው የተለያየ የመልክአ ምድር አቀማመጥና ጥሩ የሆነ የአየር ጸባይ ምክንያት ወደ ሎስአንጀለስ ፊልማቸውን ያለጫና ለመስራት ይፈልሱ ነበር።

በጣም ታዋቂ የሆነው የሆሊውድ ምልክት “hollywood” የፊልሞች መፈጠሪያ የሆነውን ያን አካባቢ የሚወክል ሆኖ በብዙ አሜሪካኖች አእምሮ ውስጥ የተቀረጸ ነው። ነገሩ እነሱን ብቻ ሳይሆን በብዙ ሚሊዮን ኪሎ ሜትሮች የምንርቀውን በባህል አስተሳሰብ አስተዳደግ የማንገናኘው እኛና አለምን በአጠቃላይ በሚባል መልኩ በአእምሮአችን ላይ ተቀርጾል።

ምልክቱ ለመጀመሪያ ጊዜ እ.ኤ.አ በ1923 የቆመ ነበር፤ ጽሁፉ ግን አሁን እንደሚነበበው “hollywood” ብቻ ሳይሆን የሚለው “hollywood land” ነበር የሚለው። ምክንያቱ ደግሞ አንድ አዲስ የሆነ የቤቶች ኮርፖሬሽን በአካባቢው ስራ ጀምሮ ስለነበር ነው። በኋላ ላይ ግን አራቱ የመጨረሻ ፊደሎቹ ጠፍተው አሁንም ድረስ እንደሚነበበው “hollywood” የሚለው ጽሁፍ ብቻ እንዲቀመጥ ተወሰ።

”የዝምታው የፊልም ዘመን“ ተብሎ ከሚታወቀው ዘመን ማለትም እ.ኤ.አ ከ1927–1948 በኋላ የሆሊውድ የፊልም ኢንደስትሪ በሃገሪቱ ያለውን የመዝናኛ ኢንዱስትሪ ተቆጣጠረው። በስሩም የሚሰሩ ትልልቅ የሆኑ የቲያትር ቤቶች ነበሩት። በዚህ ተቋም የሚሰራው ፊልም ብቻ በእነዚህ ቲያትር ቤቶች ይታዩ ነበር። ፊልሞቹ የሚሰሩበት ስቱዲዮዎች 6 ነበሩ። እስከአሁንም ድረስ ደግሞ አሉ ፓራማውንት አር ኬአ ቱዌንቲ ሴንቸሪ ፎክስ ኤም ጂ ኤም ዋርነር ብሮስ ይባሉ ነበር።

የሆሊውድ ትልቁ ለውጥ የመጣው ግን በ1950ዎቹ ከተፈጠሩት የቴሌቪዢንና የሙዚቃ መቅጃ ስቱዲዎች መፈጠር በኋላ እንደሆነ ይታመናል፤ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ነው የሆሊውድ አለም አቀፍ ተጽእኖ ፈጣሪነት የጀመረው። [1]

በአሁኑ ሰአት በሃገራችን ኢትዮጲያ በተለያዩ ቦታዎች ፊልም ቤቶች ሞልተዋል በፍላሽ <u>የፊልግነውን</u> ያህል ፊልም ገዝተን መመልከት እንድንችል ሆኗል ከ10 እና 15 አመታት

1 **steve avery.** united states history. *u-s-history.com.* [Online] 1995. http://u-s-history.com/page/h3871.html.


በሳሙኤል ክበደ youth focus telegram channal @samkb

በፊት ያልነበረውን እድል ነው አሁን በሉል አቀፋዊነት (ግሎባላይዜሽን ) ና ቴክኖሎጂ አማካኝነት የተገኘው፤ ነገሩ ግን ከጥቅሙ ጉዳቱ እጅግ ከፍተኛ ነው።

“የአገራችን ህሊናዊ በር ለሁሉም ክፋት ሆነ። በፍርሃት ይሁን በድንቁርና በጀብደኝነት ይሁን በአርቆ አስተዋይነት ለብዙ ዘማናት መክተን የያዝነው መዝጊያችን ገርበብ ብሎ ሳይሆን ብርግድ ብሎ ተከፈተ። አሁን ወልጋዳም ጎፋፋም ሃምሳ ቀንድ ያበቀለም ጭራቅ እንዳይገባ የሚከለክል ምንም ዘበኛ የለም። ደግሞ ለክፋቱ በገፍ የሚገባው የተቃናው የለዘበውና የተገራው ሳይሆን ጉዳጉድ ግሳግሱ ነው።

ድንበራችንን ዘልቆ ሲገባ በእንግዳ አክባሪ ባህላችን ተሳስቀን ተቀብለነው አገሩ ይሄዳል ስንል እዚሁ ተንፈራጥጦ ተቀመጠ። ጭራቁ ሁሉ ቤተኛ ሆነ። ለመሆኑ እዚህ አገር ክፉ አስተሳሰብና ዝቃጭ የስነምግባር አተላ እንዳይደፋ የሚከለክል ሃይ ባይ ይገኛል?

እስኪ ደግ ደጉን እንነጋገር÷ ከአለም ህብረተሰብ ስልጣኔ ተራርቃ በዚሁም ምክንያት ኋላ ቀር ሆና የኖረች ኢትዮጲያ ለእውቀት ለስልጣኔ ለስራ ትጋት ለቴክኖሎጂ ቀሰማ ለትውውቅ ለቅርርብ በዚሁም ሳቢያ ለሚገኝ የሽመታ እድል በሯን ብትከፍት ምን አለበት?ምንም ። ሉልአቀፋዊ (ግሎባል) በሆነ አለም ውስጥ በሬን ከርችሜ ስለ እድገት ማለም የትም አያደርስም ።

ገበያው ላይ ያለው እቃና አገልግሎት ብቻ በሆነ ኖሮ እጅግም አያሳስብም ነበር። አሁን ግን እየተሸጠ እየተሸመተም ያለው የአስተሳሰብ አይነትና የኑሮ ዘይቤ ነው። ከዚሁም አብዛኛው መሰረታውያን የሆኑትን የስብእና ማልሚያ እምነቶች የሚንድ ሰናያት ምግባራትን የሚያኪያኪስ መለኪያ የለሽነትን የሚያራግብ እብደትን የህይወት ፈርጥ አድርጎ የሚያሳይ የሞራል ልቅነት ሲያይ ብራቮ ! እያለ የሚያጨበጭብ ከማህበረሰብ ጤና ይልቅ ፈንጠዝያን የሚያከብር አዳዲስ የርኩሰት አራዊት የሚያራባ የክፋት ሸቀጥ ነው። ይህ ብዙ መደብሮች ቢኖሩትም የጀምላ መሸጫው ሚዲያ የሚባለው የህዝብ መገናኛ ነው። ፊልሞቻችን ሙዚቃው መጻሃፍቱ ሬድዮንው ቴሌቪዥኑ መጽሄቱ በየጓዳው በየአዳራሹ በየሜዳው ሁሉ የሚዘራው ንጽህና አምካኝ ዘር ከልካይና አስተዋይ በሌለበት ሁኔታ እያጎነቆለ ነው።

አለሙ ሁሉ በእብደት ሲሮጥ የቀደመን ስለመሰለን እነሱ በሶምሶም የሚሄዱበትን ሁሉ እኛ ኢትዮጲያውያን በሽምጥ ጋልበን ደረስንበት፤ በአንዳንድ በኩል እንዳንቀድማቸው ያሰጋል። መለኪያ የለሽነት ልክ ሆነ። ቀደም ባሉት አመታት ይህ ነጭ ይህ ጥቁር ማለት ይቻል ነበር ። ”ኧረ ነውር ነው ! “ ሲባል አዎ ነውር ነው ይባል ነበር፤ ክፋት ዛሬ የተፈጠረ ባይሆንም በስሙ ተጠርቶ ክፉ ይባል ነበር፤ ተጻራሪውም ሰናይ እጹብ ግሩም ድንቅ ማለፊያ በጎ መልካም ይባል ነበር። አሁን ግን የስነ ምግባር ዛፍ ከነስሩ ተመንገሎ ባየር ላይ ሰፈፈ። እኩይና ሰናይ የሚዳኙበት ችሎታ ተዘጋ።

” እንዴ ምን ጉድ ነው የምታወራው ምን አይነት የመአት ነቢይ መጣብን“ የሚል ሰው ይኖር ይሆን?”እንዴት የስንት ታቦት የስንት ደብር አገር የስንት መስጅድ የስንት ሼህ አገር የስንት ጸሎት ቤት የስንት ምእመናን አገር ።” ይሁና ! ይህ ሁሉ ሆኖም ሙት ሃይማኖታዎነት እንደ ሰደድ ለተዛመተው የስነ ምግባር ዝቅጠት እንደ ካንሰር ለሚራባው ሚዛን የለሽ ባህሪ


በሳሙኤል ክበዩ youth focus telegram channal @samkb

በቂ መልስ ሊሰጥ አልቻለም። ይልቁን ወርቀዘቦ የግብዝነት ካባ ስለደረበለት ውስጥ ውስጡን እየበተበተ እንዲበላን ጉልበት ሰጠው። ቤተቅዳሴ ተጣበበ እንጂ ቅዱስ ልቦና አልተገኘም፤ ማተባችን ወፈረ እንጂ ከቆዳችን አልዘለቀም፤ ቤተጸሎት የወንበዴዎች ዋሻ ሲሆን ልበ ቅኖች በፍርሃት ተሸሸጉ ጮሌዎች መንበሩን ተቆጣጠሩ። እውነት በመንገድ ጥራጊ አሰስገሰስ ታፈነች ተዳፈነች። ቤተክርስቲያን ለዘመናዊት እና ለድኅረ ዘመናዊነት የወርቅ ጥጃ ማሰሪያ ጉትቻ አዋጣች፤ ተሰርቶ ሲመጣላትም እልል አለች።"[2]

የምእራቡ አለም የራሳቸውን ምድር በርኩሰት በክፋት በጥላቻ ራስን በመውደድ በዝርፊያ የሰውን ልጅ ክብር እጅግ በሚያዋርዱ ነገሮች ሞልተውት፤ የሌላ ሃገር ልጆችን አእምሮና ሃሳብ ለማጥመድ በተንኮልና በሴራ የተሞላ መረባቸውን ወደ አፍሪካ አህጉር ከዘረጉ ሰነባብተዋል። ይህ ሆሊውድ የአሜሪካ እድገት አንዱ አካል ሆኖ ይቆጠር እንጂ ብዙ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ካመጣላቸው ጥቅም ይልቅ የወሰደባቸው መልካም ነገሮቻቸው ይበልጣል። ለምሳሌ በአንድ ጥናታዊ ጽሁፍ ላይ በአሜሪካ የሚገኙ ታዳጊዎችና ወጣቶች በመኝታ ክፍሎቻቸው የራሳቸው የሆነ ጠፍጣፋ (flat) ቴሌቪዥን አላቸው ሙሉ ቀኑን በቴሌቪዥኑ መስኮት ላይ ተጥደው ከመዋላቸው የተነሳ ብዙ ለውጦችን ያስተናገዳሉ ለአብነትም ያህል÷

<u>አካላዊ የሆነ ችግር</u>:– የእይታ የራስ ህመም የሰውነት እንቅስቃሴ መቀነስ ወደ 33% የሚሆኑት ልጆች ለክብደት መጨመር ይጋለጣሉ ይህ አሃዝ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ሄዷል።

<u>ከትምህርትና ከስራ አንጻር</u>:– የጊዜ መባከን ደካማ የሆነ የጥናት ብቃት

<u>ስነልቦናዊ</u>:– ግልፍተኛ ባህሪ አሉታዊ ምልከታ አስደንጋጭ ወይም የሚያስደነግጥ ተሞክሮ (trauma)

<u>ስሜት</u>:– ጭንቀት

<u>ባህሪ</u>:– ታላላቆችን አለማክበር ሴቶችን እንደ እቃ መመልከት ፈር የለቀቀ ንግግር

<u>አኗኗር ዘይቤ</u>:– ልክ ያልሆነ ፋሽን በጭፍኑ የፊልም ተዋኒያኖችን መከተል የእጽ አልኮል መጠጥና ማጨስን ያስፋፋል ያበረታታል።

የሚገርመው ግን አሁን በዚያች አገር ያሉ ሰዎች ሁሉ ወደዚህ አይነት የህይወት ዘይቤ የገቡበትን ቀን እየረገሙት ያሉ ይመስላሉ "መቼ ነው እንደ እ.ኤ.አ 1930ዎቹ ሰው ከቤቱ ወጥቶ፤ ከሰው ጋር የሚነጋገረው? መቼ ነው በጠረጴዛ ዙሪያ ተቀምጠው የየራሳቸው ስልክና ታብሌት ውስጥ የተቀበሩት የቤተሰብ አባላት እየተነጋገሩ እያወሩ እየተጫወቱ ማእድ የሚቆርሱት? " በሚሉ ብዙ ምኞቶችና ጥያቄዎች ተሞልተዋል። ምክንያቱ ደግሞ እንደ ቤተሰብ በአንድ ቤት ከመኖር ያለፈ የአንድነት ጊዜ መውሰድን ስለከለከላቸው ነው።

ታዳጊዎች ደግሞ እጅጉኑ ለዚህ "ካንሰር" ለሆነ በሽታ ተጋላጭነታቸው የሰፋ ነው። "ካንሰር" ያልኩበት ትልቅ ምክንያት አለኝ፤ አንዴ መመልከት ( ወደ ውስጥ ማስገባት) ከተጀመረ ሰው ሰው መሆኑ እስከሚያስረሳው ድረስ የውስጥ ማንነቱን ሰብአዊነቱን መንፈሳዊነቱን፤ ካንሰር የሰውነት የውስጥ ክፍሎችን በልቶ እንደሚጨርስ እንዲሁ ከእግዚአብሄር የተቀበልነው

2 ንጉሴ ቡልቻ፤ መስተአየት (አዲስ አበባ ፣ 2002)


በሳሙኤል ክበዴ youth focus telegram channal @samkb

ይህን መልካምነት በልቶ ስለሚጨርስ ነው። ለዚህ ማስረጃ እንዲሆን በምእራቡ አለም ያሉትን ታዳጊዎችና ወጣቶች መመልከት በቂ ነው "ለምን ተናገራችሁኝ?" "እኔ ያልኩት ብቻ ለምን አይሆንም?" "እኔ የራሴ ገገር ነኝ!" "ማንም በእኔ ህይወት አያገባውም" "ህይወቴን የምመራው እኔና እኔ ብቻ ነኝ" በወግ በባህላችን የሌለውን ታላላቆችን ያለማክበር የመናቅ እናትና አባትን መሳደብ እጅግ ልቅ መሆን ይህ ሁሉ ሆሊውድ የወለዳቸው መራራ ፍሬዎች ናቸው። እረ ጎበዝ! ሆሊውድ በልጆቻችን ላይ የተከለው የክፋት ዘር ብዛቱ! የደረሰውኛእያደረሰ ያለውም ጉዳት በቀላሉ ሊታይ የሚገባ አይደለም።

በየዩኒቨርስቲው ብንገባ "ሃይ" ባይ በሌለበት ቦታ የተመለከተውን ሁሉ በተግባር ለመፈጽም የሚዳዳው ብዙ ትውልድ አለ። አያሳዝንም? የራሳቸውን ምድር በክለውና መርዘው ሲያበቁ፤ ደግሞ የሌላውን ሃገር ትውልድ ለመበከል ውጥን ወጥነው ሲንቀሳቀሱ እየተመለከትን ለምን ዝም እንላለን? ይህ እኮ ከፋሽስት ጣሊያን ወረራ በላይ ነው የጣሊያንን የተንኮል አካሄድ የነቁበት አጼ ሚኒልክ ገፍቶ ለመጣው ጠላት :-

"እግዚአብሄር በቸርነቱ እስካሁን ጠላት አጥፍቶ አገር አስፍቶ አኖረኝ። እኔም እስካሁን በእግዚአብሄር ቸርነት ገዛሁ። እንግዲህ ብሞትም ሞት የሁሉ ነውና ስለኔ ሞት አላዝንም። ደግሞ እግዚአብሄር አሳፍሮኝ አያውቅም። እንግዲህም ያሳፍረኛል ብዬ አልጠራጠርም። አሁንም አገር የሚያጠፋ፥ ሃይማኖት የሚለውጥ ጠላት፥ እግዚአብሄር የወሰነልንን የባህር በር አልፎ መጥቷልና እኔም ያገሬን ክብት ማለቅኝ የሰውን መድከም አይቼ ዝም ብለው ደግሞ እያለፍ እንደ ፍልፈል መሬት ይቆፍር ጀመር። አሁን ግን በእግዚአብሄር ረዳትነት ሃገሬን አሳልፌ አልሰጠውም ።...."

በማለት ነበር የተነሱት፤ ሚስታቸውም እቴጌ ጣይቱ:-

"ከዚህ በኋላ ኮንት አንቶኔሊ ተናዶ ያን ትናንት የተጣፊውን ወረቀት ቀዳዶ ጥሎ ውሉን የኢጣሊያ መንግስት በጦር ሃይል እንደሚያስከብር ተናገረ። ይህን የሰሙት እቴጌ ጣይቱም ስቀው "የዛሬ ሳምንት አድርገው። በዚህ የሚደነግጥልህ የለም። ሂድ የፎከርክበትን አድርግ። እኛም የመጣውን እናነሳዋለን። እግሩን ለጠጠር ደረቱን ለጦር ሰጥቶ አገሩን የማያድን ሰው በዚህ የሌለ አይምሰልህ። የገዛ ደሙን ገብሮ ለገዛ አገሩ መሞት ጌጥ ነው እንጂ ሞት አይባልም። አሁንም ሂድ፥ አይምሽብህ፥ የፈከርክበትን በፈቀድህ ጊዜ አድርገው። እኛም ከዚህ እንቆይሃለን።" አሉት

ጣይቱ ሴት ሆነው ግን በሃገራቸው የመጣውን ዝም አላሉም

"....እኔ ሴት ነኝ። ጦርነት አልወድም። ግን እንዲህ መሳዩን ውል ከመቀበል ጦርነት እመርጣለሁ አሉ።... "[3]

"እረጎራው እረጎራው እረጎራው " ብለን ልንነሳበት የሚገባ ጉዳይ እኮ ነው። ራሱን አሳምሮና አስውቦ የደረቀ የነቀዘ ማንነቱን ሸፍኖ ወደ ሃገራችን ከገባ ቆየ።

ሰውን ሁሉ ለራሳቸው አስተሳሰብና አመለካከት ተገገር ለማድረግ፤ የሚሰሩት ስራ የተሳካላቸው <u>ይመስላል፤</u> በተለይ በተለይ ወጣቶቻችንን ታዳጊዎቻችንን ልጆቻችንን እንደ ክፉ አውሬ

3 ጳውሎስ ኞኞ፤ አጤ ሚኒልክ. (አዲስ አበባ ፣ ማንኩሳ ማተሚያ ቤት፣ 2011)


በሳሙኤል ክበደ youth focus telegram channal @samkb

ያለርህራሄ እየበላብን ነው። ገና በለጋ እድሜያቸው በእጆቻቸው የሰጠናቸው ስልኮችና ታብሌቶች፤ መልካም ያደረግን መስሎን በስጦታ ያበረከትንላቸው እቃዎች ከእግዚአብሄር መንገድ እንዲሁም ከማህበረሰባችን ሲነጥሉአቸው እያየን ነው። እንደ ቤተክርስቲያን እንደ ማህበረሰብ እንደ ሃገር አንዳችን ነገር ልናደርግ ይገባል። እነዚህ ፊር የለቀቁ ጥራዝ ነጠቅ የሆኑ የሆሊውድ ፊልሞች "ውሃ ሲወስድ እያሳሳቀ" እንዲሉ እግዚአብሄር ለሰው ልጆች ሲፈጥራቸው ከሰጣቸው መልካምና በጎ ስብእና ቀስ በቀስ ሳናውቀው ሳናስተውለው እያስፈገፈገን ነው ።

በጣም የሚያሳስበው ቀጣዩ ትውልድ ምን አይነት ይሆን ?የሚለው ጥያቄ ነው። ይህን ጸሁፍ ስጽፍ በጣም በቁጭት ውስጥ ሆኜ ነው። ምክንያቱም ብዙ ያጣናቸው፤ እያጣናቸው ያሉ የእኛ የራሳችን ልጆች ስላሉ ነው። የሱስ ማለትም የአልኮል የእጽ የአለባበስ የስርቆት የአስገድዶ መድፈር ሴትን ልጅ እንደ እቃ አድርጎ ከሚያቀርብ የሆሊውድ ፊልም የተነሳ የመጣብን በሽታ ነው፤ አሁን ላይ ያለውን ትውልድ ስንመለከት ያዩትን ፊልም ራሱን ነው የሚመስሉት በአገራችን አባባል "አይ እርሱ ቁጭ አባቱን ነው የሚመስለው" እንደሚባለው ያዩትን፤ ወደ ውስጣቸው ያስገቡትን ቁጭ ያንኑ ራሱን ፊልሙን ነው የሚመስሉት። አለባበሱ አነጋገር አካሄድ ያላቸው አመለካከት ሁሉ በሚመለከቱት ፊልሞች የተቃኘ ነው። የሃገሬ ህዝብ ሆይ ! እናቶቼ አባቶቼ እህት ወንድሞቼ ትውልዳችን ልጆቻችን ወንድሞቻችን እህቶቻችን እንዲሁ በከንቱ ሲጠፉ እያየን ዝም የምንል ከሆነ አንጀታችን ሳይራራ ለዚህ ጨካኝ አውሬ ለዚህ ክፉ ካንሰር ትውልዳችንን አሳልፈን የምንሰጥ ከሆነ እግዚአብሄርስ ዝም ይለን ይሆን? ወይስ እንደ ቃየን "ወንድምህ ወዴት ነው?" ብሎ ሲጠይቀን "እኔ የወንድሜ ጠባቂ ነኝን?" ብለን እንመልስ ይሆን ?ስለ "ምን አገባኝ" ሳወራ አንድ ጽሁፍ ትዝ አለኝ÷

"ልጆች ሳለን ከብጤዎቻችን ጋር በየአጋጣሚው ስንጋጭ ከሚሰነዘሩ አባባሎች አንዱ "ምን አገባህ?"የሚል ነበር።"ምን አገባህ?" የተባለውም "ሚስት" በማለት መልስ ይሰጣል፤ ወይም "አንተን አማክሬ ነው የማገባው?!" ይላል። ይህን መሳይ አባባሎች በልጅነት ያከተሙ ይመስለኝ ነበር፤ ተሳስቻለሁ ።

ችግሮች ሲፈጠሩ የተፈጠሩትን ችግሮች በግልጽ የሚናገር "አንተ ምን አገባህ?" ይባላል፤ አሁንም ። "አብዛኛው ሰው የሚሞተው በማያገባው እየገባ ነው" ተብሎ ይመከራል ። ድንበሩን እያለፈ የሰዎችን የግል ጉዳይ ውስጥ የሚገባ ሰው "ምን አገባህ?"ቢባል ብዙም አያስደነግጥም፤ በአገር ወይም በእግዚአብሄር ቤት ጉዳይ ሲሆን ግን ያስደነግጣል ። አባባሉ ሰዎች እነርሱን በግል የሚጎዳ ነገር ካልደረሰባቸው በቀር ግዴለሾች እንዲሆኑ የሚገፋፋ ነው። "[4]

እኔም ይህ ጉዳይ የእግዚአብሄር እናም የሃገር ጉዳይ ነውና "በምን አገባህ?"ና "ምን አገባኝ" መታለፍ የለበትም ባይ ነኝ።

በከተሞቻችን በየዩኒቨርስቲዎቻችን የምንመለከተው ጥፋትና ክፋት ሁሉ ከዚህ ጥራዝ ነጠቅ ከሆኑ ፊልሞች የመነጨ ናቸው። እንደነሱ በቸልተኝነት የዘራነውን ከማጨዳችን በፊት፤ በቶሎ በአፋጣኝ መፍትሄ ልንፈልግ ይገባል።

4 ጳውሎስ ፈቃዱ፤ የብርሃን አንጓዎች(አዲስ አበባ ፣ ርኖበት አሳታሚዎች፣ 2006)


በሳሙኤል ክበዩ youth focus telegram channal @samkb

ጌታ ኢየሱስ ጻፎችና ፈሪሳዊያንን እንደ ገሰጸው

“እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳዊያን በውጭ አምረው የሚታዩ በውስጡ ግን የሙታን አጥንት ርኩሰትም ሁሉ የተሞሉ በኖራ የተለሰኑ መቃብሮችን ስለምትመስሉ ወዮላችሁ” ማቴ 23÷27

ብሎ እንዳለው ይህ ፊልምም እንደዚሁ ነው ከውጭ አምሮ በውስጡ ግን አጥንት የሆነ ከውጭ ተውቦ ውስጡ ግን የነቀዘ ለትጠላት ምቹ የሆነ ትውልድ አምካኝ መሳሪያ ነው። አሁን አሁን አዲስ አባባችን በነዚህ የሆሊውድ ርኩሰት ነጋዴዎች ተሞልታለች። ምን አዲስ አበባ ብቻ መላው ሃገራችን ሁሉ። ቀስ በቀስ የእውነትን አምድ ወደምትጠብቀው ቤተክርስቲያን ሳይገባ፤ መፍትሄ ሊበጅለት ይገባል። እነሱ እግዚአብሄርን ለማወቅ ባልወደዱት መጠን ለክፉ አሳብ አሳልፎ ጌታ የሰጣቸው ናቸው። በዛ በክፉ ሃሳብ የሰሩትን ርካሽ ነገር ለአለም ሁሉ በግፍ እየቸበቸቡ ነው። ሴት እህቶቻችንና ልጆቻችን ለማይገባ ብዝበዛ እየተዳረጉብን ነው። ገና በልጅነታቸው ልጅ እያረገዙ፤እግዚአብሄርም ያሰበላቸው ሃሳብ እየጨነገፉ እነርሱም ካሰቡት ሳይደርሱ ባልጠበቁት መከራ ተይዘዋል።

ያላቻ ጋብቻን በጽኑ ብንቃወምም ግን ሆሊውድ እያቀረበ ካለው የክፉት የርኩሰት ገበታ ልንታደጋቸው፤ እሱንም በጽኑ ልንቃወም አልተቻለንም።

“አንድ አዲስ ጓደኛ አፈራሁ። ከዚህ ጓደኛዬ ጋር እፍ ብለን ውጥተን ወርደን ዘለን ፈርጠን ሲመሽ ወደ ቤታችን አቅጣጫ የሚወስደውን መንገድ ይዘን ጎን ለጎን እያወራን እናዘግማለን፤ ድንገት ጓደኛዬ የማልጠብቀውን እንግዳ ነገር መፈጸም ይጀምራል። መንገድ ላይ ያሉ የደረቁ የውሻ ኩሶች እያነሳ ወደ አፉ ልኮ ይቆረጥማል። መጀመሪያ በመገረም ባየውም ጥቂት ቆይቼ ”ከለማበት የተጋባበት“እንዲሉ እኔም እንደሱ ከመሬት እየለቀምኩ የውሾቹን ኩስ መቃም ጀመርኩ። የጎረስኩትን ሳልውጥ ገና ባፌ ሳለ ድንገት ባንኜ ከእንቅልፌ ነቃሁ። ለካስ በህልሜ ነው። ክእንቅልፌ ስነቃ ድርጊቱን ከመጸየፌ የተነሳ ራሴን ያገኘሁት ጣቶቼን አፌ ውስጥ አስገብቼ ምላሴን ለመቧጠጥ እየዳዳኝ አፌ ተከፍቶ እጄ አፌ ስር ተንከርፍፎ ነበር። ሰአቱን ስመለከት ውድቅት ሌሊት ነው። የገዛ ሰውነቴ ቀፈፈኝ። ለጥቂት ደቂቃዎች አልጋ ላይ ሆኜ የህልሙን ዘግናኝነት እያሰብኩ ከቆየሁ በኋላ ከአልጋ ወርጄ እግዚአብሄር ከክፉ እንዲታደገኝ በጸሎት ተማጸንኩና ተመለሼ ተኛሁ።

ከዚያ ህልም የተነሳ ያን ሰሞን በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ የምተዋወቀውን አዲስ ሰው ከሌላው ጊዜ በተለየ ጥንቃቄ እመለከት ጀመር። ከህልሙ እንደተረዳሁት አዲስ ወደ ህይወቴ የሚመጣና የመይሆን ነገር የሚያለመምደኝ ሰው እንደሚኖር ተገንዝቤያለሁ። ስለዚህ ያን ሰሞን ”ይሄ ሰው ይሆን?“ “ያ ሰው ይሆን?”ስል ቆየሁና አንዳች የተፈጠረ ነገር ስላልነበር ቀስ በቀስ ህልሙንም ጥርጣሬውንም ረሳሁት።

ከወራት በኋላ እንደ ልማዴ ለአገልግሎት ወደ ተባበሩት የአረብ ኤሜሬቶች አቀናሁ።... ልመለስ አንድ ቀን ሲቀረኝ ከጋበዘችኝ ቤተክርስቲያን አገልጋይ ጋር የንግድ ሱቆች አካባቢ ዞር ዞር ስንል አንድ ያልጠበቅኩት ውድ እቃ ቅናሽ ወጥቶ አገኘሁ። እቃውን ለመግዛት የቀደመ እቅድ ባይኖረኝም አጋጣሚውን ማለፍ አልፈለኩም። እጄ ላይ የነበረውን ገንዘብ አሟጥጬ ገዛሁት። እቃው ”ሆም ቲያትር“ የሚባል በርካታ ድምጽ ማጉያዎች ያሉት የዲቪዲ ማጫወቻ


በሳሙኤል ክበዴ youth focus telegram channal @samkb

ነው። በጊዜው አለ የሚባል ምርጥ እቃ ነበር። በነጋታው በኢትዮጲያ አየር መንገድ አስጭኜ ወደ አገሬ በረርሁ። በብዙ ጣጣ ከጉምሩክ ካወጣሁት በኋላ ወደ ቤቴ አቀናሁ።

በተመለስሁ በማግስቱ መሳሪያዎቼን አዘገጃጅቼ መመሪያውን በመከተል መገጣጠም ጀመርኩ። ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ ብጨርስም የድካሜን ውጤት ለመየት አልቻልኩም። ምክንያቱም በቤቴ ውስጥ ማጫወቻውን የምሞክርበት ዲቪዲ አልነበረኝም። ስለዚህ ከተማ ወጣሁና ዲቪዲ ማከራያ ሱቅ ፈለጌ ፊልም እንዲያከራዩኝ ጠየኩ። ማከራያ ቤት ውስጥ ያገኘኋት ወጣት የመንን ፊልም እንደምፈልግ ጠየቀችኝ። እውነት ለመናገር ከዚያ በፊት እምብዛም ፊልም አይቼ ስለማላውቅ የምላት ጠፋኝ። ታዋቂ የፊልም ኮከቦች እየጠራች ልታስመርጠኝ ሞከረች። እስካፍር ድረስ አንዳቸውንም አላወኳቸውም። ቢቸግረኝ "አንቺ ጥሩ ነው የምትይውን ስጪኝ"አልኳት። እሷም "ጥሩ ነው" የምትለውን ሰጠችኝ። ይዤ ወደ ቤት ነዳሁና ዲቪዲውን አስገብቼ ከግራ ከቀኝ ከፊት ከኋላ በሚመጣ ማሳጭ ድምጽ እየተደመምሁ ብቻዬን ፊልሜን መኮምኮም ቀጠልሁ። ፊልሙ አፍ የሚያስከፍትና ልብ የሚያንጠለጥል የአንድ ቤተሰብ ታሪክ ነበር። እኔም ታሪኩ መስጦኝ የሶፋው ጫፍ ላይ ተቀምጬ ስመለከት ድንገት በመሃል በዘዴ የተከሸኑ የወሲብ ትእይንቶች ይመጡ ጀመር። ገቢሮቹ በተከፈተው የአእምሮዬ ከርስ ሰተት ብለው ሲገቡ ታወቀኝ።

ጥቂት ቆይቶ በውስጤ÷ "ባለፈው ያየኸው ህልም ይህ ነው። አዲሱ ባልንጀራህ ይህ እቃ ነው። ከመንገድ እየለቀምህ የበላህውም የውሻ ኩስ የሆሊወድ ውሾች የጣሉት ርኩሰት ነው"... ወዲያው ተንበርክኬ በህልሜ እንዳየሁት የበላሁትን የሆሊውድ ውሾች ኩስ በንስሃ መትፋትኝ የተዋስኩትንም መመለስ ነበረብኝ።" [5]

ወንጌላዊ ያሬድ ጥላሁን የሆሊውድን እርኩሰት ከህይወቱ የገጠመውን በእደዚህ ውብ መልኩ ተርኮልናል እኔም ከሰሞኑ ያስተዋልኩትን ላካፍላችሁ። ይህን ጽሁፍ በምጽፍበት ጊዜ "game of thrones" የተባለ ተከታታይ ፊልም የሁሉንም ታዳጊና ወጣት ቀልብ የያዘበት ጊዜ ነው። ፊልሙ HBO (home box office) በተባለ የአሜሪካ ቴሌቪዥን ኔትወርክ ላይ በተከታታይነት የሚተላለፍ ነው። እስከ ዛሬ በHBO ኔትወርክ ታሪክ ከተላለፉ ተከታታይ ፊልሞች እጅግ ታዋቂ ከሆኑት መካከል አንዱ ነው። በአማካይ ከ23 ሚሊዮን በላይ ተመልካች አሉት ተብሎ ይገመታል። በኛም ሃገር ከጥቂት ሳምንታት በፊት ለመጀመሪያ ጊዜ በአዲስ አበባ ከተማ በማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ የመጨረሻው ክፍል የሚወጣበት ወቅት ተጠቅሶ በትልቁ ተለጥፎአል፤ ይህ ምን ያህል ሆሊውድ ሰርጎ እየጋባ እንዳለ የሚያሳይ ነው።

ፊልሙ ፈጽሞ እርባና ቢስ በሆኑ ነገሮች የተሞላ ነው። የሚያስተላልፈው መልእክት ከንቱነትን እንዲንሰራፋ፤ የትውልድን አእምሮ እንዲያስር እንጂ ምንም ርባን ወይም ጠብ የሚል ጥቅም የለውም። ጌታ የሰጠንን እድል ጊዜ ህይወት አእምሮ እንዳንጠቀም በከንቱ ነገር የተሞላን ፊልም በማየት እንድንጠፋ፤ በሃጢአት ህይወታችን እንዲሞላ ከአምላክ ፊት ሸሽተን እንድንኮበልል መንገድ ከፋች ሆኖ ሆሊውድም እንዲ ባሉ ፊልሞቹ ትውልድን የማምከን ስራውን እየሰራ እንታዘባለን። ጠላታችን ዲያብሎስ ሳንነቃበት ይህን ኢንዱስትሪ ትውልድን ወደ ራሱ ካዝና ገቢ እያደረገበት ነው።

5 ወንጌላዊ ያሬድ ጥላሁን፤ እፎይታ ካልአይ ( አዲስ አበባ ፣ ርኖቦት፣ 2011)


በሳሙኤል ክበደ youth focus telegram channal @samkb

ጠንካራ መጽሃፍትን በመጻፍ የሚታወቁት የ ዲዛየርኢንግ ጎድ ኦርጋናይዜሽን(desiringGod.org) መስራች የሆኑት ጆን ፓይፐር የ"game of thrones" ፊልምን ከመመልከታችን በፊት ልንጠይቃቸው የሚገቡ 12 ጥያቄዎች ብሎ ከጻፈው ጥቂቱን እንመልከት።

- ቅድስናን የሚገልጥ ወይም በበለጠ እንድቀደስ የሚያደርግ ነው ወይ?

"ዳሩ ግን፡፡ እኔ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ ተብሎ ስለ ተጻፈ የጠራችሁ ቅዱስ እንደ ሆነ እናንተ ደግሞ በኑሮአችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁኑ ።" 1ጴጥሮስ 1:15

"እንግዲህ፥ ወዳጆች ሆይ፥ የዚህ ተስፋ ቃል ካለን፥ በእግዚአብሔር ፍርሃት ቅድስናን ፍጹም እያደረግን ሥጋንና መንፈስን ከሚያረክስ ሁሉ ራሳችንን እናንጻ። " 2ቆሮንቶስ 7:1

- ዛሬ ለመንግስተ ሰማይ አይኔን ካላወጣሁ መቼ ላወጣ ነው?

"ቀኝ ዓይንህም ብታሰናክልህ አውጥተህ ከአንተ ጣላት፤ ሙሉ ሰውነትህ በገሃነም ከሚጣል ይልቅ ከአካላትህ አንድ ቢጠፋ ይሻልሃልና። "ማቴዎስ 5:28–29

- ክቡር የሆነውን ማሰብ ማሰላሰል በቂ አይደለም ወይ?

"በቀረውስ፥ ወንድሞች ሆይ፥ እውነተኛ የሆነውን ነገር ሁሉ፥ ጭምትነት ያለበትን ነገር ሁሉ፥ ጽድቅ የሆነውን ነገር ሁሉ፥ ንጹሕ የሆነውን ነገር ሁሉ፥ ፍቅር ያለበትን ነገር ሁሉ፥ መልካም ወሬ ያለበትን ነገር ሁሉ፥ በጎነት ቢሆን ምስጋናም ቢሆን፥ እነዚህን አስቡ፤" ፊልጵስዩስ 4:8

- እግዚአብሄርን ለማየት አልጓጓሁም ወይ?

"ልበ ንጹሖች ብፁዓን ናቸው፥ እግዚአብሔርን ያዩታልና።"ማቴዎስ 5:8

- ልጄ እንደዛ እራቁቷን ሆና ብትተውን ደስ ይለኛል ወይ?" [6]

ለነገሩ እነዚህ ጥያቄዎች የትኛውንም ፊልም ከመመልከታችን በፊት ልንጠይቅ ይገባናል ብዬ አስባለሁ።

ጳውሎስ በዚያን ዘመን ለሮሜ ሰዎች ሲጸፍላቸው÷ልክ እንደሆሊውድ አእምሮአቸውን ስለተነጠቁት ሰዎች እንዲ ባለመልኩ ይገልጻቸው:-

"ስለዚህ እግዚአብሄር ለሚያስነውር ምኞት አሳልፎ ሰጣቸው፤ ሴቶቻቸውም ላባህርያቸው የሚገባውን ስራ ላባህርያቸው በማይገባው ለወጡ፤ እንዲሁም መንዶች ደግሞ ለባህሪያቸው የሚጋባውን ሴቶችን መገናኘት ትተው እርስ በርሳቸው በፍትወት ተቃጠሉ፤ ወንዶችም በወንዶች ነውር አድርገው በስህተታቸው የሚገባውን ብድራት በራሳቸው ተቀበሉ።" ሮሜ 1:26–27

ጳውሎስ ሰይጣን አእምሮአቸውን እንዴት እንደነጠቃቸው ይነግረናል። አሁንም በዘመናችን የወንድ ለወንድና የሴት ለሴት ጋብቻ በምእራቡ አለም ተስፋፍቷል። ይህን የርኩሰት ስራቸውን ወደ ሃገራችን ለማስገባት ብዙ ሞክረው ባይሳካላቸው፤ በፊልም ግን የብዙዎችን አእምሮ

6 **reinke, tony.** desiring God. *desiring God.com.* [Online] 5 20, 2014. https://www.desiringgod.org/articles/twelve-questions-to-ask-before-you-watch-game-of-thrones.


በሳሙኤል ክበዩ youth focus telegram channal @samkb

እየሰረቁ ነው። የሃገራችንን ድንበር የሚጠብቁ ውድ የሆኑ የሃገራችን ልጆች አሉ። ተደብቆ ሊገባ የሚችልን ነገር የሚመረምሩ የደህንነት አካላትም አሉን። ግና በገሃድ ራሱን አስውቦ እየገባ ያለውን ይህን የትውልድ ጸር ሊለዩልን የሚችሉ እግዚአብሄርን በፍጹም ልባቸው ሃሳባቸው ነፍሳቸው የሚወዱ ጀግና የሆኑ የመንግስቱ ወታደሮች ያስፈልጉናል። ይህ በመንፈሳዊ መቃኛ (ስካነር) ካልተቃኘ ዘመን ባመጣው መሳሪያ ተመርምሮ ህጋዊነትን አግኝቶ ወደ ሃገራችን እየገባ ነው። በመንፈስ የሚመሩና የሚመረምሩ መቃኘት (ስካን) ማድረግ የሚችሉ ወታደሮች ያስፈልጉናል።

ጳውሎስ አእምሮአቸው የተወሰደባቸው ሰዎች ምን እንደሚመስሉ በዚሁ በሮሜ መጽሃፍ ምእራፍ 1 ላይ በሚደንቅ ሁኔታ ይገልጻቸዋል።

" እግዚአብሄርን ለማወቅ ባልወደዱት መጠን እግዚአብሄር የማይገባውን ያደርጉ ዘንድ ለማይረባ አእምሮ አሳልፎ ሰጣቸው፤ አመጻ ሁሉ÷ ግፍ÷ መመኘት÷ ክፋት ሞላባቸው፤ ቅናትን÷ ነፍስ መግደልን÷ ክርክርን÷ ተንኮልን÷ ክፉ ጠባይን ተሞሉ፤ የሚያሾከሹኩ÷ ሃሜተኞች አምላክን የሚጠሉ÷ የሚያንገላቱ÷ ትእቢተኞች÷ ትምክህተኞች÷ ክፋትን የሚፈላለጉ÷ ለወላጆቻቸው የማይታዘዙ÷ የማያስተውሉ÷ ውል የሚያፈርሱ÷ ፍቅር የሌላቸው÷ ምህረት ያጡ ናቸው÷ እንደዚህ ለሚያደርጉት ሞት ይገባቸዋል የሚለውን የእግዚአብሄርን ህግ እያወቁ እነዚህን ከሚያደርጉ ጋር ይስማማሉ እንጂ አድራጊዎች ብቻ አይደሉም።" ሮሜ 1:28–32

የሆሊውድን ርኩሰት ወደ አእምሮአቸው የሚያስገቡ ሁሉ ቀስ በቀስ ሳያውቁት ወደዚህ የባህሪይ የሞራል የመንፈሳዊ ህይወት ውድቀት ውስጥ መግባታቸው ሳይታለም የተፈታ ህልም ነው። እሺ መፍትሄው ምንድን ነው? ምንስ እናድርግ?

<u>ስቀሉኝ ስቀሉኝ</u>

አለም ስትቋምጥ ግሳንግሷን ይዛ
ሸቀጧን ሸክፋ ወሰኔ ተጉዛ
ልትጋልበኝ ሽታ ጀርባዬ ላይ ወታ
ልቤን ተቆጣጥራ ልትሆንብኝ ጌታ

መስቀል ላይ ቢታየኝ ሞቼ ተቸንክሬ
ሁሌም ከምትገዛኝ ለምኞቷ ኖሬ
ሬሳዬ ተሰቅሎ በስብሶ ቢሸታት
ጠረኑ ቀርንቶ መቆሚያ ቢያሳጣት
ተስፋዋ መና ሆኖ ካላሁበት ሰፈር
እፍረት ተከናንባ ከእኔ ትሸሽ ነበር

እኔም ህያው ሆኜ ከሷ ከምወዳጅ

ምኞቴ አይሎ ሁሉን ከምጎመጅ

አንቅሬ ልተፋት ላላያት ላታዬኝ

መስቀል ነው ድንበሬ የሚገላግለኝ

ውርደቱን ባታይ ነው አይ ሞኙ ቢሉኝ

ለእኔስ ጌጤ እርሱ ነው ስቀሉኝ ስቀሉኝ !!!

ግጥም በባይሳ ገመቹ

የካቲት 23 2012

# ሰናይ ሳምንት



በሳሙኤል ክበዴ youth focus telegram channal @samkb